**ልጅዎ የቋንቋ፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታዋን እንድታሻሽል የሚከተሉትን እንቅስቃሴዎች ይጠቀሙ፤**

- ልጅዎ ከተወለደችበት ቀን አንስቶ ያነጋግሯት። በጨቅላ እድሜዋ የቋንቋ ድምጾችንና የንግግር ዜማዊ ድምጾችን ትማራለች።
- ልጅዎ ለመናገር በመሞከር የምትፈጥራቸውን ድምጾች ለመረዳት ይሞክሩ። ለመነጋገር እየሞከረች ስለሆነ ሊያበረታቷት ያስፈልጋል።
- በቃላት ይጫወቱ፡ ተመሳሳይ ዜማ ያላቸው ቃላትን በመጠቀም፣ የማይረቡ/ሞኝ አባባሎችን፣ እንዲሁም የህጻናት ቀልዶችን ይጠቀሙ።
- ለልጅዎ በየቀኑ ያንብቡ። ልጆች ከጨቅላ እድሜያቸው አንስቶ ሲያነቡላቸውና ስእሎችን በመጠቆም/ማዛመድ እንዲሁም አዳዲስ ቃላት በመስማት ይማራሉ፤ እንዲሁም አብሮ በማንበብ የሚያሳልፉት ጊዜ በጣም ይጠቅማል።
- ከልጅዎ ጋር በሚያነቡበት ጊዜ ልጅዎን ጥያቄዎች ይጠይቁ፤ ስለስእሎችና በሚቀጥለው ገጽ ምን ሊፈጠር እንደሚችል የልጅዎን ግምት ይጠይቁ።
- ለልጅዎ ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ገና እየሞነጫጨረች ቢሆንም፣ አንዳንድ ዝርዝሮችን፣ ታሪኮችን፣ እንዲሁም ምልክቶችን መጻፊያ መሳሪያዎችን ያቅርቡ።
- ለልጅዎ በሌሎች ሰዎች መካከል ስትሆን ልጅዎን ወክለው ከመናገር ወይም ከማጣደፍ ይልቅ በራሷ እንድትናገርና ምላሽ እንድትሰጥ እድል ይስጧት።

8.

የግል እና ማህበረሰባዊ እድገት/መጎልበት

የግል እና ማህበረሰባዊ እድገት/መጎልበት አንድ ልጅ ስሜቱን እንዴት በሚገባ መግለጽ እንዳለበት፣ ከሌሎች ጋር እንዴት መግባባት እንዳለበት፣ እንዲሁም የራሱን በዚህ አለም ላይ መገኘት እርግጥ መሆኑን እንዲገነዘብ የሚረዱ ችሎታዎችን ያጠቃልላል። የልጆች የግል እና ማህበረሰባዊ እድገት/መጎልበት ከወላጆች እና ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት የተመሰረተ ነው። ይህም አንድ ልጅ ስለራሱ ያለው ስሜት፣ ልጁ ስለራሱ ተማሪነት ያለው አመለካከት፣ እንዲሁም ስለራሱና ስለሌሎች ስላለው ሃላፊነት ያለውን ስሜት ያጠቃልላል።

9

**ልጅዎን  የግል እና ማህበረሰባዊ ችሎታዎችን እንዲያዳብር ሊረዱት ይችላሉ**
- ህጻን ልጅዎ በሚያለቅስበት ጊዜ ምላሽ ሊኖርዎት ይገባል። ይህም ልጅዎን እንደሚወዱትና በእርስዎ እንክብካቤ እንደሚያገኝ ለልጅዎ ያረጋግጥለታል።
- ልጅዎን ለማቀፍና ለመንካት የሚያገኙትን አጋጣሚዎች በተቻለ መጠን ይጠቀሙ። የልጅዎን ፊት በመመልከት በለስላሳ ድምጽ ያነጋግሩት። ይህም ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲጠነክርና ልጆች ይህንን በጥሩ መልኩ እንዲቀበሉ ይረዳቸዋል።
- ልጅዎን አዳዲስ ነገሮች እንዲሞክር ያበረታቱት፤ በሙከራውና እንዲሁም በስኬታማነቱ ይደሰቱ- (በመጀመሪያ እርምጃዎቹ፣ በራሱ ለመጀመሪያ ጊዜ መመገብ ሲችል፣ የመጀመሪያ ቃላቱን ሲናገር፣ ወዘተ.)
- በልጅዎ ጥረት ያለዎትን ደስታና ኩራት ልጅዎ የሳላቸውን ስእሎች በቤትዎ ውስጥ ግድግዳ ላይ ወይም ምግብ ማቀዝቀዣ ፍሪጅ ላይ በመለጠፍ ያሳዩ።
- ልጅዎ ያለውን ስሜት እንዴት ማድረግ እንዳለበት (ለምሳሌ ከሌላ ሰው ጋር አለመስማማት ሲፈጠር፣ ወዘተ...) ያሳዩት። የሌሎችንም ስሜት እንዲረዳ ያስተምሩት።
- ለልጅዎ የአንዳንድ ችግሮችን መልስ ወይም መፍትሄን ከመንገር ይልቅ ተገቢ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲሁም ስለነገሩ እንዲያስብ በማድረግ መፍትሄ እንዲያገኝ ያግዙት።

10

የሂሳብ ችሎታ

የሂሳብ ትምህርት ዋና መሰረቱ ቁጥሮችን፣ መለኪያ፣ የተወሰነ ፀባይ ያላቸው (ለምሳሌ የተወሰነ ዝምድና ያላቸው) ነገሮችን፣ እንዲሁም ቅርጾችን መረዳት መቻል ነው። ልጆች የጀማሪ ሂሳብ ጥያቄዎችን መልስ ለማግኘት እነዚህን ጽንስ ሃሳቦች መጠቀም አለባቸው።

11

**ወላጆች ልጆቻቸውን የሂሳብ ችሎታ እንዲያዳብሩ ሊረዷቸው ይችላሉ።**

- በየእለቱ የሚጠቀሟቸውን አንዳንድ ነገሮች፣ የልጅዎን ጣቶች (ልጅዎን በሚያጥቡበት ጊዜ) ፣ ልጅዎን በሚያለብሱበት ጊዜ የልብሱን ቁልፎች፣ እንዲሁም ሲራመዱ የእርምጃዎትን ቁጥር ይቁጠሩ።
- በመጠን የሚበላለጡ ነገሮችን ይጠቁሙ-(መጻህፍት፣ አሻንጉሊቶች፣ ጫማዎች፣ ወዘተ…)
- እቃዎችን በቀለምና በመጠን ለይተው ያስቀምጡ- ለምሳሌ ሰማያዊ ቀለም ያላቸውን የእግር ሹራቦች ወይም የልጅዎን ከነቴራዎች፣
- የአንድ ነገርን (የአቀማመጥ፣ ቅርጽ፣  ወይም የተከታታይ ቁጥር ጸባይ) ለልጅዎ ይግለጹ፣ እንዲሁም ልጅዎን ቀጥሎ ምን አይነት ቅርጽ እንደሚከተል፣ ወይም በሚቀጥለው ከነቴራ ወይም በጨሌ ጌጥ ላይ ምን አይነት ንድፍ ሊኖር እንደሚችል ይጠይቁ።
- ለልጅዎ መጠንና ቦታን የሚገልጹ ንግግሮች - የበለጠ፣ ያነሰ፣ ከታች፣ ከላይ፣ ወዘተ… በመጠቀም ያስረዱ።
- በየእለቱ የሚገለገሉባቸው ነገሮች ቅርጾችን ለልጅዎ ይግለጹ- ለምሳሌ የቁርስ ሲሪያልስ ካርቶን አራት ማእዘን መሆኑንና ሲሪያል የሚበላበት ጎድጓዳ ሳህን ጫፉ ክብ መሆኑን ለልጅዎ ይንገሩ።
- ምግብ በሚሰሩበት ጊዜ እንዴት የመለኪያ እቃዎችን (ማንኪያ እና ኩባያዎችን) እንደሚጠቀሙ ያሳዩ። ቁመቷንም በርዝመት መለኪያ ይለኩ።
- በእለቱ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ቅደም ተከተል ከልጅዎ ጋር ያውሩ ፦ “ከምሳ በኃላ መናፈሻ ፓርክ እንሄድና ቀጥሎም ወደ ሱቅ/ገበያ እንሄዳለን።”

12

የሳይንስ ችሎታ

የሳይንስ ችሎታ አካባቢን የመመርመርና የጥያቄ መጠየቅ አስፈላጊነትን ያጠቃልላል። ልጆች አለማቸውን በማየት፣ በመግለጽ፣ ጥያቄ በማቅረብ፣ እንዲሁም መደምደሚያ ላይ በመድረስ እንዲመረምሩ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

13

**ልጅዎን በሚከተሉት መንገዶች የሳይንስ ችሎታውን እንዲያዳብር ሊረዱት ይችላሉ፤**

- ውጪ በእግር አብራችሁ ተንሸራሸሩ፣ አንዳንድ ድምጾችን፣ ሽታዎች፣ እንዲሁም የምታዩትን ነገሮች ተገንዘቡ
- ልጅዎ በአሸዋ እና ውሃ እንድትጫወት ያድርጉ
- ስለአየሩ ሁኔታ ከልጅዎ ጋር ያውሩ፣ ልጅዎም የአየር ለውጥ እንድትገምት ይገፋፉ
- ልጅዎ የቤት እንስሳትን፣ ወፎችን፣ እንዲሁም ሌሎች እንስሳትን እንድታይና እንድትገነዘብ ያበረታቱ፣ ስለጸባያቸውም ተወያዩ
- ልጅዎ ማወቅ ስለምትፈልገው አታክልትና እንስሳት የበለጠ እንድትማር ይርዷት
- ውጪ የሚገኙ አንዳንድ ነገሮችን ለምሳሌ ድንጋይ፣ ቅጠላቅጠሎች፣ አበቦች፣ እና የበሉጥ ዛፍ ፍሬ (ኤኮርን) ለልጅዎ ያሳዩ
- የማጉያ መነጽር፣ የርቀት መመልከቻ መነጽር፣ እና ማስመሪያ አንዳንድ ነገሮችን ለመመርመር ይጠቀሙ
- ልጅዎ አንዳንድ ነገሮች እንዴት በፍጥነት ወይም በቀስታ እንደሚሄዱ፣ የትኞቹ ነገሮች እንደሚንሳፈፉ እና የትኞቹ እንደሚሰምጡ፣ እንዲሁም ውሀ እንደሚቀዘቅዝና በረዶ እንደሚሆን ያስተምሩ።

14

የህብረ-ትምህርት

የህብረ-ትምህርት ልጆች ዙሪያቸው ስላለው አለም ያላቸውን እውቀት ይመለከታል። የራሳቸውን ከሌሎች መለየት፣ እንዲሁም ከሌሎች ጋር ያላቸውን ልዩነቶች ማወቅና ልዩነቶቹን በማድነቅ እንዲሁም በአለም ላይ ስላሉት ልዩልዩ ባህሎች መማር ይጀምራሉ።

15

**ልጅዎን በሚከተሉት መንገዶች የህብረ-ትምህርት ችሎታውን እንዲያዳብር ሊረዱት ይችላሉ፡**

- ቤተሰብዎ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ስላሉት መመሳሰልና ልዩነቶች ከልጅዎ ጋር ያውሩ፦ በቤተሰቡ ውስጥ ስላሉት የልጆች ቁጥር፣ ቁመታቸው፣ ዕድሜአቸው፣ ወዘተ…
- የቤተሰብዎ አባላት ስላላቸው ልዩልዩ ስራዎች ከልጅዎ ጋር ይወያዩ
- ልጆችዎ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎችን በመምሰል እንዲማሩ ያግዟቸው--ለምሳሌ አስተማሪ፣ ሀኪም፣ ወይም የሱቅ ሰራተኛ
- በሰፈራችሁ ያሉ አንዳንድ ሱቆች አብራችሁ በመሄድ ስለሱቁቹ፣ ጫማ ቤት፣ መድሃኒት ቤት፣ ወዘ፡ ያውሩ።
- የእንቅልፍ ሰአት፣ ልብስ በጋራ መካፈልና የመሳሰሉ ቤተሰብ ህጎች ያውጡ፤ እንዲሁም ተወያዩበት።
- ከልጅዎ ጋር የሰፈር ጽዳት አብራችሁ ተካፈሉ፤ እንዲሁም ጠቀሜታውን ለልጅዎ ያስረዱ።
- ልጅዎን በአካባቢው ያሉ ለምሳሌ መጻህፍት ቤቶች፣ ቤተ-መዘክር(ሚውዚየም)፣ ወይም የታሪካዊ ማህበር፣ እና መናፈሻዎች ይውሰዱ።

16

ጥበብ

ጥበብ የልጅዎን ውዝዋዜ(ዳንስ ጭፈራ)፣ ተውኔት፣ ስነ-ጥበብ፣ እና ሙዚቃ እውቀትን ያጠቃልላል። ልጆች የሚያይዋቸው ነገሮችን ቦታ በመስጠት መማርና መሳተፍን ያጠቃልላል።

17

**ልጅዎን በሚከተሉት መንገዶች ጥበብ ችሎታውን እንዲያዳብር ሊረዱት ይችላሉ፡**

- ከልጅዎ ጋር አብረው ይዘምሩ ወይም ይዝፈኑ፤ የዘፈኑን ምቶችን በማጨብጨብ ይጠቁሙ።
- ሙዚቃ ይጫወቱ፤ ልጅዎም አብራ እንድትጨፍር(እንድትደንስ) እና እንድትዘፍን/እንድትዘምር ያበረታቱ
- ልጅዎ አብራ ሙዚቃ እንድትጫወት አንዳንድ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ የእንጨት ማንኪያዎች፣ የፕላስቲክ ምግብ ማስቀመጫዎች፣ ድስቶች) ያቅርቡ።
- በየቀኑ ስዕል ለመሳል የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ለልጅዎ ያቅርቡ። ስለሰራችው ስእል ወይም ሌላ ነገር እንድትነግርዎ ይጠይቋት።
- ልጅዎ የምትወደውን ታሪክ በመምሰል እንድትጫወት፣ እያንዳንዳችሁ ልዩልዩ የታሪኩን ተጫዋች ክፍል በመውሰድ ተጫወቱ።
- ልጅዎን ልዩልዩ የሙዚቃ ዝግጅቶች፣ የዳንስ ጭፈራ ዝግጅቶችን፣ የጥበብ ዝግጅቶች ይውሰዱ። እነዚህም በማህበረሰብ መሰብሰሚያ ቦታዎች፣ የሃይማኖት መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ ውጪ የሚካሄዱ ትርኢቶችና በአላት፣ እና የመገብያ አዳራሽ (ሞል) በመሳሰሉ ቦታዎች በነፃ መመልከት ይቻላል።

18

የሰውነት አካል መጎልበት እና ጤንነት

**ለፕሮግራማችን መሰል በመሆን እንዲሁም የ ሲ.ቲ.ኬ (CTK) ምልክትን ለመጠቀም ስለፈቀዱልን ምስጋና ያቀርባል።**

Countdown to Kindergarten: Learning Begins at Birth
Maryland's Early Childhood Public Engagement Campaign
608 Water Street
Baltimore, Maryland 21202

www.countdownMD.org

© 2004 Maryland Committee for Children
**ህትመት**: © 2004 Bonnie Matthews